# የቢጋሻው ደሳለኝ ሐራጥቃዊ ማንነት!

እኛ የዚህ ዘመን ሰዎች በምሥጢር ከበሰሉት፣ ከጠነቀቁት፣ ከነቅዓ ንጹሕ ከጠጡት፣ ሥርዓት ይዘው ከሚሰብኩት ወይም ከሚያስተምሩት፣ እውነቱን ከሚናገሩት ሊቃውንት አባቶች ይልቅ በመደንፋት፣ በማጉራት፣ ወሬ አጣፍጦ ቀምሞ በማውራት፣ በመደለል በመሸንገል የሚሰብከው ነገር ግን በምሥጢር ያልበሰለው ጥራዝ ነጠቁ ወመኔ ይስበናል ይማርከናል፡፡ ጥራዝ ነጠቅ ማለት ጥልቀት፣ ስፋት፣ ጥብቀት፣ ደርዝ፣ መሠረት የሌለው ግልብ ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እነኝሁ ወሬ አጣፍጠው ማውራት የሚችሉቱ ጥራዝ ነጠቆቹ በርካታ ተከታይና ደጋፊ ማፍራት ችለዋል፡፡ ጥራዝ ነጠቆቹ በርካታ ደጋፊና ተከታይ ለማግኘታቸው ሌላም ዋነኛ ምክንያት አለ፡፡ ይሄንን በምሳሌ ባስረዳ ይቀለኛል፡፡

ታሪኩ ከ 15 ዓመታት በፊት የተፈጸመ ታሪክ ነው፡፡ ታሪኩ በካሴት (በክር ወይም በቅርፀተ ድምፅ) ታትሞ በየመዝሙር ቤቱ ይሸጥ ስለነበረ ይሄንን ታሪክ ብዙዎቻችሁ ታውቁት ይሆናል ብየ እገምታለሁ፡፡ አንዲት ሳባ ሐጎስ የምትባል ቀንደኛ መናፍቅ ነበረች፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ያለ መናፍቅ ሳባ ሐጎስን የማያውቅ አልነበረም፡፡ ቦንኬ የተባለው ነጭ የመናፍቃን ዓለምአቀፍ ሰባኪ ባለመፈጸሙ ሐሰትነቱ የታወቀበትን ትንቢት እየተናገረ ሀገራችን መጥቶ በነበረበት ጊዜ "ብቸኛዋ ልሳን ተርጓሚ!" ሲል በሐሳዊ አንደበቱ የመሰከረላት ከባድ የመንፈሱ አገልጋይ ነች ሳባ ሐጎስ ማለት፡፡

መናፍቃን ልሳን ተገለጠልን የሚሉት በየቃልቻ ቤቱ፣ በየ ዛር ቤቱ ቃልቻው፣ ባለዛሩ ያደረባቸው ክፉ መንፈስ ድንገት ሲለውጣቸው በኃይልና በስሜት ተሞልተው የሚያንተረትረው እራሱ ተናጋሪው ሌላም ሰው ትርጉሙን የማያውቀውንና ከሰው ልጆች ቋንቋ ውጭ የሆነውን የኢጋንንትን ድምፅ ነው ልሳን የሚሉት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን **"ልሳን ተገለጠላቸው!"** የሚለው ሐዋርያቱ በሚያስተምሩበት ሰዓት ከተለያዩ ሀገራት መጥተው ኢየሩሳሌም የነበሩ የተለያዩ ሀገራት ሰዎችን ቋንቋ ሐዋ. **2፥1-13,** እና በሐዋርያት ዘመን ሐዋርያት በሰበኩባቸው ሀገሮች ክርስትናን የተቀበሉ ወገኖች መንፈስ ቅዱስ የራሳቸው ከሆነው ቋንቋ ሌላ የሌሎችን ቋንቋዎች ነው **1ኛ ቆሮ. 14፥1-33** ልሳን የሚለው እንጂ ትርጉሙ ምን እንደሆነ የማይታወቀውንና የሰው ልጆች ቋንቋ ያልሆነውን አጋንንት በባለ ዛሩና በቃልቻው ላይ አድሮ የሚያኾጎደጉዱትን የቃላት ሩምታ እነሱንም ያደረባቸው ጋኔን እንዲያኾጎደጉዱት የሚያደርጋቸውን የኢጋንንት ድምፅ ማለት አይደለም፡፡

እናም ያኔ በዚያን ጊዜ ይህች ልጅ ልክ ወደ አዳራሻቸው ስትገባ አንድም ሰው ከመቀመጫው ላይ አይገኝም ነበረ፡፡ ግማሹ ይዘላል፣ ግማሹ እየጮኸ ይንከባለላል፤ ግማሹ እየተወራጨ ያለቅሳል አዳራሹ ቀውጢ ነው የሚሆነው፡፡ ከአንደበቷ ቃል ያወጣች ጊዜማ ሌላ ነገር ነው የሚሆኑት፡፡ የራሷ መኪና ከሾፌር ጋራ ተሰጥቷት ነው የምትንቀሳቀስ የነበረው፡፡ ይህች ልጅ አንድ ዲያቆን ወንድም ነበራትና እሱን ለማመንፈቅ ጥረት ታደርግ ነበረ፡፡ ልጁ ግን ቃል ተናግሮ መከራከር አይችልም ነበረና አልችላት ቢል ወይም መከራከር ቢያቅተው ምን ይላታል ከሚያገለግልበት የቅዱስ ሚካኤል ደብር ጸበል ነበርና እየጨቀጨቀች ስታስቸግረው "እኔ ካለሁበት ቤተክርስቲያን ነይና ጸበል ውስጥ ገብተሽ ምንም ሳትሆኝ ከወጣሽ ተከትየሽ እሔዳለሁ!" ይላታል፡፡ እሷም "ውይ ደሞ ለውኃው ነው እንዴ!" ትልና መኪናዋን አስነሥታ ካለበት ድረስ ከች ትላለች፡፡

ጸበሉ ውስጥም ገባች፡፡ እግዚአብሔር ተአምሩን ሊገልጥ ፈቃዱ ነበርና ጸበሉ ውስጥ ስትገባ ደኅና የነበረችው ልጅ ልክ ጸበሉ ሲነካት ማጉራት መንፈራገጥ ጀመረች፡፡ ለካ በኑፋቄ ያደረባትን ጋኔን ቅዱስ ሚካኤል ፈጥርቆ ይዞት ኖሯል፡፡ ከዚያማ ስንቱን ጉድ መለፍለፍ ጀመረ፡፡ ልጆች መቅረጸ ድምፅ አምጥተው የተጋለጠው መንፈሷ የሚለፈልፈውን ነገር

መቅዳት ጀመሩ፡፡ ይሄ እርኩስ መንፈስ መናፍቃንን እንዴት እንዴት እያደረገ እንደሚጫወትባቸው፣ ለተንኮሉ ተአምራትን እንደሚያሠራቸው በርካታ ምሥጢሮችን ለፈለፈ፡፡ ብዙ ነገር ለፍልፎ ለፍልፎ ለቀቃት፡፡

እጅግ የሚገርመው ነገር መንፈሱ ሲለቃት ልጅቱ መናፍቅ ከመሆኗ በፊት ወደነበረችበት ማንነቷ ነው መልሷት የሔደው፡፡ ልጅቱ እንኳንና ያ እንደጉድ የምታንበለብለውን መጽሐፍ ቅዱስ ይቅርና አንዲት ጥቅስ እንኳ የማታውቅ ሆና ቁጭ አለች፡፡ ለካ በአንደበቷ አድሮ መጽሐፍ ቅዱሱን እንዲያ ያንበለብለው የነበረው ይሄ ያደረባት ክፉ መንፈስ ኖሯል ለካ፡፡ እሱ ደፋር አይደል የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ ሳይቀር እየጠቀሰ ለመፈታተን የሞከረ ቀጣፊ እኮ ነው፡፡ ዛሬም በሰው ላይ አድሮ ጥቅስ እየጠቀሰ ለማሳሳት ቢሞክር የሚደንቅ አይሆንም፡፡ ለዛም ነው ልጅቱ እሱ ሲለቃት ምንም የማታውቅ ልትሆን የቻለችው፡፡ ሰው መናፍቅ ሲሆን እዚያ አዳራሽ ከመግባቱ አንደበቱ ጥቅስ በጥቅስ የሚሆንበት ምክንያት ሥልጠናውና ትምህርቱ ሳይሆን ምሥጢሩ ይሄው ነው፡፡

እናም የሐራጥቃ ተሐድሶዎችን ወይም የመናፍቃንን አንደበት እንዲያ እያሰላና ጠባያቸውን እያለሰለሰ፣ የዓለም ሰው ሊሳብ በሚችልበት ቅንና ትሑት አቀራረብ አንደበታቸውን እያጣፈጠ የሚያናግራቸው እርኩስ መንፈስ እንጅ እነሱ ራሳቸው ሰዎቹ አይደሉም፡፡ ልላቹህ የፈለኩትና ይሄንን ምሳሌ ያመጣሁበት ምክንያት ሰይጣን ሰውን እንዴት መሳብ እንደሚችል ያውቅበታልና ነው እንደ በጋሻው ያሉ ሐራጥቃ ተሐድሶዎች ወይም መናፍቃን ዓለማዊ ሰዎችን መሳብ የሚችሉትና በርካታ ደጋፊዎችን ለማፍራት የቻሉት ማለቴ ነው፡፡ ለዚህም ነው የእግዚአብሔር ቃል፦

"...እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል!" **2ኛ ቆሮ. 11፥13-15**

"መንፈስ ግን በግልጥ። በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል!" 1ኛ ጢሞ. 4፥1 በማለት እውነቱን ቁጭ አድርጎ የሚያስጠነቅቀን ለዚህ ነበር የሚሰማ ቢኖር፡፡

ከዓመታት በፊት ነው ወደ አንድ ገዳም ሔድኩ፡፡ አንድ ቀን ከአንደኛው መናኝ ቤት አምስት ሆነው ከነሱ ውስጥ አንዱ እንደኔ ለመጠየቅ ከከተማ የሔደ ነው፡፡ በዎክማን (በተራማጅ ሰው) መቅረጸ ድምፅ "የመማፀኛ ከተማ!" የሚለውን የበጋሻውን ካሴት (ክር ወይም ቅርጸተ ድምፅ) እያዳመጡ አገኘኋቸው፡፡ ያሏቸው ክሮች በሙሉ የበጋሻው ስብከቶች ናቸው፡፡ በዚያ ዘመን በጋሻውን እንደኔ ያሉ ሰዎች ይጠረጥሩት ነበር እንጅ ዛሬ በተጋለጠበት ደረጃ ገና አልተጋለጠም ነበር፡፡ ከዛ እኔ "አይ ወንድሞቸ የበጋሻውን ስብከቶች ባታዳምጡ መልካም ነው፡፡ ልጁ ግልጥ አልወጣም እንጅ ችግር ያለበት ሰው ነው፣ በምሥጢርም የበሰለ አይደለም!" አልኳቸው፡፡ ትንሽ ተጨቃጨቅን፡፡

ከዛ እንደኔ ለጥየቃ ከከተማ የመጣ ነው ያልኳቹህ ልጅ "ልታናግረው ትፈልጋለህ እንዴ?" ብሎ ጠየቀኝና ሞባይል ስልኩን (ተንቀሳቃሽ መናግሩን) አውጥቶ ደወለና ስፒከር (ማጉያ) ላይ አድርጎ ሰጠኝ ስልኩን ያስኩና "ማንን ነው የማናግረው?" እያልኩ የስልኩን መነሣት ጠበኩ፡፡ "በጋሻውን ነዋ!" አለኝ፡፡
ስልኩ ተነሣና በጋሻው "ሃሎ!" አለ፡፡ እኔም መልሸ "ሃሎ በጋሻው እንዴት ነህ?" አልኩትና ገዳም ለጥየቃ በመጣሁበት ባንተ ጉዳይ ትንሽ ተጨቃጨቅን፡፡ እንደኔ ለጥየቃ ከመጣው ሰው ጋር ለካ ትተዋወቁ ኖሯል "ልታናግረው ትፈልጋለህ እንዴ?" ብሎ ደወለና ነው ስልኩን ያስያዘኝ!" አልኩት፡፡

በጋሻው ሳቅ አለና "እሽ ምንድን ነው ታዲያ ልታናግረኝ የፈለከው ጉዳይ ምንድን ነው ያጨቃጨቃቹህ?" አለኝ፡፡ እኔም "ጥሩ አንተን በተመለከተ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ጥያቄ የፈጠሩብኝ ነገሮች አሉ ከእነዚያ ውስጥ አንዱን እጠቅሳለሁ፡፡ "አይ!" ካልከና ካስተባበልክ መረጃየን እጠቅሳለሁ፡፡ "አዎ!" ከሆነ ደግሞ ምላሽህ ግልጽ እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ!" አልኩት፡፡ "መልካም ምንድነው ጥያቄ የፈጠረብህ ጉዳይ!" ሲል ጠየቀኝ፡፡ በርካታ መናኝ ከቦ ያዳምጠናል፡፡ እኔም "ጥሩ

እኛ ተዋሕዶዎች የምንጠራው የምናመልከው ኢየሱስ እና መናፍቃን የሚጠሩት የሚያመልኩት ኢየሱስ አንድ ነው ብለህ ታምናለው ወይ?" ስል ጠየኩት፡፡ እሱም አላንገራገረም "አዎ!" ሲል መለሰልኝ፡፡

እኔም "በጣም ጥሩ ስለዚህ መረጃ መጥቀስ አያስፈልገኝም ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ ግን ይሄንን ትምህርት ከየት አመጣኸው? ቤተክርስቲያን ይሄንን ብላ ታስተምራለች? እንደማታስተምር እናውቃለን፡፡ ወንጌሉም የሚለው ክርስቶስ አንድ እንደሆነና በኋለኛው ዘመን ግን በሐሰተኞች መምሕራንና ሐሰተኞች ነቢያት በየእልፍኙ (በየአዳራሹ) የሚሰበኩ ሐሰተኞች ክርስቶሶች እንደሚመጡ ነው የሚናገረው ማቴ. **24፥3-28**፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ኤፌ. **4፥5**, ጢሞ. **4፥1**, ዕብ. **13፥8** ፣ የያዕቆብ ወንድም ሐዋርያው ይሁዳ ይሁ.**1፥3** ፣ ነቢዩ ኤርሚያስ **6፥16** ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ እንደሆነ፣ ሃይማኖትም አንዲት እንደሆነች ተናግረዋል፡፡

ዛሬ ላይ ግን በክርስትና ስም ብቻ እንኳ የሚጠሩ ሃይማኖት ነን ባይ ድርጅቶች ከ 33 ሽህ አልፏል፡፡ ሌሎቹ ሲጨመሩ ደግሞ ቁጥራቸው የትየለሌ ነው፡፡ ቃሉ ግን አንዲት ሃይማኖትና አንድ ጌታ ብቻ እንዳለ ተናግሯልና ከነዚህ ሁሉ ትክክለኛዋና እንድንባት፣ ለነፍሳችን እረፍት እናገኝበት ዘንድ የተሰጠችን መንገድ ወይም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለክባት ሃይማኖት አንዷ ብቻ ናት ማለት ነው፡፡ የተቀሩት ግን አይደሉም ወይም ሐሰተኞች ናቸው ማለት ነው፡፡ ቃሉ የሚለው ወይም ቤተክርስቲያን የምታስተምረው ይሄንን ከሆነ አንተ ከየት አምጥተህ ነው መናፍቃን የሚጠሩትና የሚያመልኩት ኢየሱስ ክርስቶስና ተዋሕዶ የምትጠራውና የምታመልከው ኢየሱስ አንድ ነው ልትል የቻልከው?" ስል ጠየኩት፡፡

እሱም አሳጥሮ "እነሱም የሚያምኑት አንድ ኢየሱስ ብቻ መኖሩን ነው!" ሲል መለሰ፡፡ እኔም ""እንዴ ምን እያልክ ነው በጋሻው? ቃሉ ከላይ የጠቀስኩትን ብሎ ያጋልጣቸዋል እንጅ እነሱማ ታዲያ "በቁጥራችን ልክ 33 ሽህ ዓይነት ኢየሱስ ነው ያለው፣ አዎ ኢየሱስ አንድ ስለሆነና ሃይማኖትም አንዲት ስለሆነች ከዚህች ከአንዷ ውጭ የተቀረነው የምናመልካቸውና የምንሰብካቸው የተለያዩ ኢየሱስ ክርስቶሶች ጌታ በወንጌሉ ይመጣሉ ያላቸውን ሐሰተኞችን ኢየሱሶችና ኢየሱስ ነኝ ብሎ የሚመጣውን አውሬውን ነው የምንጠራውና የምናመልከው!" ሊሉ ኖሯል እንዴ ታዲያ? በምሳሌ ላስረዳህ ልሞክር፡- ለምሳሌ አንተ በጋሻው አለህ ወፈር፣ ጠቆር ያልክና መካከለኛ ቁመት ያለህ ሰው ነህ፡፡ ሔጀ ለጓደኞችህ "ያ ቀጭኑ፣ ቀዩ ረጅሙ ጓደኛቹህ በጋሻው እንዴት ነው? ደኅና ነው ወይ?" ብየ ብጠይቃቸው አንተን ነው ወይ የገለጽኩት? ከስምህ በስተቀር ሌሎች የጠቀስኳቸው መገለጫዎች አንተን የሚገልጹ ናቸው ወይ?"" ስል ጠየኩት፡፡

እሱም "አይደለም!" ሲል መለሰ፡፡ እኔም "በጣም ጥሩ የዚህን ያህል ልዩነት አለው እኛ የምንጠራውና የምናመልከው ኢየሱስ መናፍቃኑ ከሚጠሩትና ከሚያመልኩት ኢየሱስ ጋር፡፡ በሰጠሁህ ምሳሌ ከስምህ በስተቀር ሌሎች ያንተ መገለጫዎች ናቸው ብየ የጠቀስኳቸው መገለጫዎች ያንተ እንዳልሆኑና አንተን እንዳልገለጹ ሁሉ መናፍቃንም ከስሙ በስተቀር "የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጫ ነው!" ብለው የሚጠሩት መገለጫ ሁሉ እሱን የሚገልጹና የሱ መገለጫዎች አይደሉም፡፡ አንዱ "አሁንም አማላጅ ነው!" ሲለው ሌላው "ሚካኤል ነው!" ይለዋል፡፡ አንዱ "በብሉይ አብ ነበረ በሐዲስ ወልድ ሆኖ መጣ የማዳን ሥራውን ሠርቶ ሔደ አሁን መንፈስ ቅዱስ ሆኖ በመሀላችን ይኖራል!" ሲል ሌላው "እንደ እኛ ሰው ነው በመልካም አገልግሎቱ ተመርጦ ተቀባ እንጅ!" ይለዋል፡፡ ሌላውም ሌላ ሌላውም ሌላ ይለዋል፡፡ ከስሙ በስተቀር ሁሉም ስለ ኢየሱስ ማንነት የሚናገሩት የአንዱ ከሌላው ይለያያል አንድ አይደለም፡፡ አንድ ቢሆን ኖሮ ሲጀመር መለያየቱም ባልተፈጠረ ነበረ፡፡ አንድ በሆኑ ነበረ፡፡ ስለሚለያዩ ወይም አንድ ስላልሆኑ ነው የተለያዩት፡፡

ስለሆነም ሁሉም ኢየሱስ ስላሉ ብቻ አንዱን ኢየሱስን ነው ሁሉም የሚጠሩት የሚያመልኩትም ልንል አንችልም፡፡ ክርስቶስም በወንጌሉ "ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይመጣሉ!" ሲል የተናገረው ይመጣሉ ብሎ ባላቸው በየዕልፍኙ (በየአዳራሹ) በሐሰተኞች መምህራንና በሐሰተኞች ነቢያት የሚሰበኩትን የተለያዩ ዓይነቶችን ክርስቶሶች ነው፡፡ በሒሳብ ፈተና ላይ ፈተናውን እንድናልፍ የሚያስችለን በፈተናው ወረቀት ላይ የሒሳብ ፈተና መሆኑን መጻፍ ሳይሆን የቀረቡ ጥያቄዎችን ደምረን፣ ቀንሰን፣ አባዝተን፣ አካፍለን በትክክል መመለስ ነው ሊያሳልፈን የሚችለው!"" ስል አብራራሁለት፡፡

ከዛ በጋሻው ሆይሻ እንዳላዋጣው ሲገባው ዞር አለና ምን አለ መሰላቹህ "እኔ እኮ ፓስተሮችን ሳይቀር አሳምኜ ያስጠመኩ

ሰው ነኝ!" ብሎ አረፈው፡፡ እኔም "እንዴ በጋሻው የሚያመልኩት ኢየሱስ ተዋሕዶ የምታመልከውን ኢየሱስ ነው ብለህል፡፡ እዛው ሳሉ የሚጠሩትና የሚያመልኩት ኢየሱስ ትክክለኛውን ኢየሱስ ከሆነ ምን አጥተው፣ ምን ፈልገው፣ ምን ሊያደርጉ ነው የሚጠመቁት? ምንስ ነው የሚያምኑት?" ስል ጠየኩት፡፡ እሱም "አይ መንገዳቸው ትክክል ስላልሆነ ነው!" አለ፡፡ እኔም "ምኑ ነው ትክክል ያልሆነው? መንገዳቸው ከእውነተኛውና ትክክለኛው ኢየሱስ ክርስቶስ ካደረሳቸው እንዴት ነው ትክክል የማይሆነው?" ስል ጠየኩት፡፡ በጋሻው ከዚህ በኋላ ሊለው የሚችለው ነገር አልነበረም፡፡ ዝም ጭጭ ብቻ ሆነ ምላሹ፡፡

ከዛ እኔ "ይህ አስተሳሰብህ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ የሚፃረር ስለሆነ ከዚህ አስተሳሰብህ ውጣ!" እያልኩ ስናገረው በመሀል ገባና "ግን እንዲህ ብየ እንደማምን እንዴት አወክ? ማለቴ ቅድም መረጃ ያልከው ምን ነበረ?" ሲል ጠየቀኝ፡፡ እኔም ""ከዓመታት በፊት "የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች!" ስትል ባሳተምካት አነስተኛ መጽሐፍ ላይ "ትናንትና በየአደባባዩ፣ በየፌርማታው፣ በየመንገዱ የኢየሱስን ስም ያለ ፍርሐት በድፍረት ይጠሩ የነበሩ አንደበቶች ምነው ዛሬ ደከሙ..." ምናምን ይላል፡፡ ይሄንን ቃል ሳይ በየመንገዱ ኢየሱስ ኢየሱስ የሚሉት መናፍቃን ናቸውና "እንዴ! ይሄ ልጅ መናፍቃንን ነው እንደዚህ የሚለው ማለት ነው? መናፍቃን የሚጠሩትና የሚያመልኩት ኢየሱስ እኛ ወይም ቤተክርስቲያን ከምንጠራውና ከምታመልከው ኢየሱስ ጋር አንድ ነው ብሎ ያምናል ማለት ነው?" ብየ እንድጠይቅ አደረገኝ፡፡ ይሄው ግምቴም አልሳተ በቃልህም አረጋገጥክልኝ!"" ስል መለስኩለት፡፡ እሱም "በል እሺ ስለደወልክልኝ አመሰግናለሁ!" ብሎ ተሰናበተኝ፡፡ ይሄንን ሁሉ ነገር ከቦ ይሰማን የነበረው መናኝ ሁሉም የበግዋሻውን ማንነት ከአንደበቱ ተረድቷልና ከዚያ በኋላ የበግዋሻውን ስብከት ብቻ አይደለም መጠቀሚያው የሚያደርጋቸውን ምንም የማያውቁትን የነ ዘርፌን፣ የበጋሻው ድምፅ ያለበትን መዝሙር ሁሉ አልቀራቸውም ልቅምቅም አድርገው አውጥተው ጣሉት፡፡

በጋሻው ግን "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ አይቀርም!" እንዲሉ ከዚያ በኋላ ባለው ሕይዎቱ ከዚህ ክርክራችን ሊማር፣ ሊመከር፣ ሊለወጥ ሳይችል ቀርቶ ጭራሽም ብሶበት እራሱን የበለጠ ግልጽ አድርጎ ወጣ፡፡ ከአባቶች እግር ስር ቁጭ ብሎ የተማረውና ያደላደለው ምሥጢር ስለሌለው፣ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ልብ ወለድ ድርሰት አንብቦ መተረክ ስለሆነ የሚያውቀው እንደመሰለው በተናገረ ቁጥር በሚናገረው ነገር ላይ በርካታ ስሕተቶች ወይም ኑፋቄዎች መገኘታቸው ግድ ሆነ፡፡ "ኧረ ባክህ እንደዚህ አይደለም ታረም!" ሲባልም ራሱን አንቱ ብሏልና "በጋሻው ተሳስቶ ታረመ!" ከሚባል ሰማይና ምድር ቢገለባበጡ የሚመርጥ ሆነ፡፡ ራስን ማምለክ ትርፉ ይሄው አይደል!፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም እንደመሰለን የምንተረጉመው ተራ መጽሐፍ አይደለም፡፡ የሊቃውንቱን ትርጉምና አስረጅነት አስተማሪነት የሚፈልግ በምሥጢር፣ በተወሳሰበ ቃል የተሞላ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ እንደመሰለን እንተርጉም ሲባል ነው ከ 33 ሺህ በላይ ሐሰተኛ የእምነት ድርጅቶች በክርስትና ስም ሊፈለፈሉ የቻሉት፡፡ በጋሻው መጨረሻ ላይ መሰንበቻውን እንደሰማቹህት "ሃይማኖት የሚባል ነገር የለም! ሃይማኖት የለኝም! የሚያድነው በኢየሱስ ማመን እንጅ በተቋም መታቀፍ አይደለም! የእምነት ተቋማት የሰዎች ሥራ ናቸው!" ሲል አሁንም ድንቁርናውንና ታላቅ ክህደቱን አረጋገጠ፡፡ አስገራሚው ነገር ልጁ እስከዛሬ ድረስ የሃይማኖትን ምንነት አለማወቁ ነው፡፡ ሰው ሃይማኖት ሳይኖረው በኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ በአባቱ በአብና በጰራቅሊጦስ መንፈስቅዱስ ሊያምን አይችልም፡፡ ያለ ሃይማኖት እንዴት ኢየሱስን ማግኘትና ማመን እንደሚቻል በጋሻው ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸው ጥቅሶች አንዲት ሃይማኖት መኖሯንና ለነፍሳችን እረፍትን ልናገኝ፣ ኢየሱስን ልናመልክ የምንችለው በእርሷው እንደሆነ ከዚህ የወጣው ትምህርት ግን የአጋንንት እንደሆነ ሐዋርያት እየተናገሩ እንዴት እንዲህ ይባላል? ሃይማኖት ባይኖር ነው እንዴ ሐዋርያቱ "ወንድሞች ሆይ! ስለምንካፈለው ስለመዳናችን ልጽፍላቹህ እጅግ ተግቸ ሳለሁ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኳቹህ እጽፍላቹህ ዘንድ ግድ ሆነብኝ!" ሲሉ ሐዋርያቱ የተናገሩት? ሃይማኖት ስለሌለ ነው እንዴ "በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ!" **1ኛ ጢሞ. 4፥1** ሲሉ ሐዋርያቱ የተናገሩት**?** ሃይማኖት ስላለና እንደነበጋሻው የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን የሚክዱና የሚያስክዱ የአጋንንት አጋልጋዮች ስላሉ፣ እኛ ግን ሃይማኖትን ለመጠበቅ እንድንጋደል አይደለም ወይ ሐዋርያት እንዲህ ሲሉ በግልጽ የተናገሩትና ያስጠነቀቁት? እነ በግዋሻው ይሄንን የእግዚአብሔር ቃል የት ሊጥሉት ነው "ሃይማኖት የሚባል ነገር የለም ይሄ የሰዎች ሥራ ነው!" የሚሉት? ዳሩ እንደሳባ ሐጎስ ያደረበት የኑፋቄ ወይም የክህደት ጋኔን ያስለፈልፈዋል እንጅ ምን እንደሚናገር እሱ ራሱስ

ቢሆን መች ያውቀውና!

እነ በግዋሻው ብቻ አይደሉም ኢጋንንት አስርገው ያስገቧቸው ነጣቂ ተኩሎች፡፡ ሌሎች በርካታ ተኩሎችም ተሰግስገው አሉ፡፡ በጳጳሳት ደረጃ ሁሉ ቦታ ለመያዝ በቅተዋል፡፡ ሲኖዶስ ነኝ በሚለው በአራት ኪሎው የጳጳሳት ቡድን ውስጥ እና ውጭ በስደት ባለው ሲኖዶስ ውስጥ ቦታ ይዘው እየፋነኑ ያሉበት አደገኛና አስደንጋጭ ሁኔታ ነው ያለው፡፡ እነኝህ መናፍቃን እኛ የምናደርገውን ተኩሎቹን ከበጎች መንጋ እየለየን የማስወጣቱን፣ የማባረሩን፣ የማስወገዱን ተግባር "ክርስቶስ የሞተለትን በግ ከበረት ማስወጣት ክርስቶስ ለምን እንደሞተ አለመረዳት፣ የክርስቶስን መሥዋዕትነት ከንቱ ማድረግ ነው!" እያሉ ተኩላትን ለይተን በማራቅ ክርስቶስ የጣለብንን የእረኝነት አደራና ተግባራችንን እንዳንወጣ ይሄንን በማለት አሞኝተው ሊያዘናጉና በጎችን በትጋት ለመንጠቅ እንዳንችል ለሚያደርጉት የማሳቀቅና ሽንጋይ ጥረት ጆሮ ሳንሰጥ ካህናትና ምእመናን በመተባበር ተኩላትን ከመንጋው እየለየን የማስወጣቱን ሥራ ተግተን እንድንቀጥልበት አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ ይሄንን ማድረግ ካልቻልን በአኃት አብያተክርስቲያናት የደረሰው አደጋ ኪሳራና ውድመት በእኛም ቤተክርስቲያን ላይ እንደሚደርስ ልንጠራጠር አይገባም፡፡

ተኩላ ተኩላ እንጅ በግ አይደለም አይሆንምምና ተኩላትን ስናሳድድ ፈጽሞ ሐዘኔታና የመሳቀቅ ስሜት ሊሰማን አይገባም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ **"...**እያለቀስኩ እላቹሀለሁ፣**...** ከእነሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ**!"** ሮሜ**. 16፥15,** ፊል**. 3፥18** ብሎ አስጠንቀቀ እንጅ "እነሱም እኮ ክርስቶስ የሞተላቸው ናቸው ተዋቸው!" አላለም፡፡ ክርስቶስ ደጋግሞ ያስጠነቀቀው ቁምነገርና እረኝነት ማለትም ተኩላትን ከበጎች ከመንጋው እንዳይደርሱ አድርጎ ማሳደድ፣ ከመንጋው ማራቅ፣ መለየት፣ በጎቹ እንዳይበሉ ተግቶ መጠበቅ ማለት ነውና ፈጽሞ በተኩሎቹ አስመሳይ የማዘናጊያና የማሳቀቂያ ቃል ተደልለን ልንዘናጋና ተኩሎቹ ከመንጋው ጋር ተቀላቅለው እያየን ባሉበት ልንተዋቸው አይገባም! ይሄንን ያደረገ እረኛ ቢኖር ተኩላን ከመንጋው ቀላቅሎ በጎችን አስበልቷልና ወዮታ አለበት፡፡ ይሄ የክርስቶስን አደራ መብላትና ባለዕዳ መሆንም ነው እጅግ እንጠንቀቅ! መናፍቃኑ እንዲህ እያሉ እያጃጃሉ ነው የሕንድን፣ የአርመንን፣ የሶርያን አኃት አብያተክርስቲያናትን ለመከፋፈል ለመሰንጠቅ የቻሉት፣ የግብጽን ቤተክርስቲያን ከመሠረቱ የበከሉት፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለ ወላዲቱ ድንግል ወለ መስቀሉ ክቡር አሜን**!!!**

ድል ለቤተክርስቲያን!!! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com